# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 16 ጥቅምት 20 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## የሠራተኛ ማኅበራት የሀገር ግንባታ ሚና



# ቀዳሚ ሥራችንና ኃላፊነታችን ሰላም ማረጋገጥ ይሁን !

የሀገራችን ሰላም ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ይገኛል። በጥላቻ በሚነዱ ኃይሎች እጅ የዜጎች ሕይወት እየተቀሰፈ ነው፤ ኢትዮጵያዊያዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የማይችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ተጠያቂነት ያለባቸው የማይመስላቸው ኢመደበኛ ስብስቦች በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ይፈርዳሉ፤ ፍርዱንም ራሳቸው ያስፈጽማሉ፣ ይፈጽማሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት የሚታወቀው መንግሥት ዜጎችን ሲጨቁን ነው። በጥላቻ የተደራጁ ኢመደበኛ ስብስቦች ሕዝብን የሚጨቁኑበት አግባብ በኢትዮጵያ አይታወቅም፤ አለ ቢባልም ከተደራጀ ዝርፊያና የመንደር ሽፍታነት ያለፈ ልምድ የለንም። አሁን እየመጣ ያለው ዓይነት የቡድን ጭቆና ኢትዮጵያዊያን የማናውቀው ነው።

በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ደግሞ መንግሥት ራሱ በቡድኖች ጭቆና ስር እየወደቀ መሆኑ ነው። መንግሥት ሥርዓት የማስከበር አቅሙ በበቂ ደረጃ ላይ ያለ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት ማየትና መጠበቅ የሚገባው መንግሥታዊ ሥርዓት አደጋ ውስጥ እየገባ ነው።

ሰላም ከሌለ ስለ ብልጽግና መናገር ፋይዳ የለውም። ሰላም በሌለበት ስለ አካባቢ ጥበቃ (Environment) መጨነቅ ትርጉም የለውም። ሰላም ከሌለ የፓለቲካ ፉክክር የለም። ሰላም ከሌለ ሀገር የለም። በአሁኑ ሰዓት ከሰላም ማስከበር የምናስቀድመው አንዳችም አጀንዳ ሊኖረን አይገባም።

በአሁኑ ወቅት የመንግሥት ቀዳሚ ሥራ የሕዝብና የሀገር ሰላም ማረጋገጥ ነው ብለን እናምናለን። መንግሥት ሥርዓት የማስከበር ኃይሉን እንዲያጎለብትና በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲያውል እንጠይቃለን። ከመንግሥት በተጨማሪም ኃላፊነት የሚሰማቸው የፓለቲካ ድርጅቶችም ሁሉ ቀዳሚ ሥራቸው ሰላም ማስከበርን መደገፍ መሆን ይኖርበታል ብለን እናምናለን።

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) መንግሥትና ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዲሁም የሚመለከታቸው የኅብረተሰብ አባላት የተሳተፉበት፤ ባለሙያዎች ሙያዊ ምክራቸውን የሚያቀርቡበት የሰላም ጉባኤ እንዲዘጋጅ ጥሪ ያደርጋል።

መንግሥት በአፋጣኝ ወደ ህግ ማስከበር ሥራ እንዲገባና አጥፊዎችን ወደ ፍርድ እንዲያቀርብ ኢዜማ በድጋሚ ይጠይቃል። እየመጣው ያለው አደጋ መንግሥትንም ይዞት የሚጠፋ መሆኑ ባለስልጣኖች እንዲገነዘቡና አፋጣኝ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያሳስባል።

**ቀዳሚ ሥራችንና ኃላፊነታችን ሰላም ማረጋገጥ ይሁን! ከሁሉም ነገር በፊት ሰላም !**

# ኢዜማ በሲያትልና በሎስአንጀለስ ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ

ጥቅምት 20 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ጥቅምት 16 እና ጥቅምት 17 ቀን 2012 ዓ.ም በሲያትል እና በሎስ አንጀለስ ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባ ማካሄዱን የኢዜማ ዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪ ኢዮብ መሳፍንት ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

የስብሰባዎቹ ዓላማዎች ኢዜማን ማስተዋወቅ፣ ብዥታዎችን ማጥራት፣ ደጋፊዎችን ማሰባሰብና መመልመል እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብ መሆኑን ተጠሪው አስረድተዋል፡፡ በስብባዎቹም ላይ እሳቸውና የፓርቲው ምክትል መሪ አንዱዓለም አራጌ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡ ከውይይቱ ታዳሚያንም የኢዜማ ፕሮግራምና ደንብ ምን ይመስላል? በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ኢዜማ ያለው አቋምስ ምንድን ነው? ወደፊትስ ኢዜማ ምን ለመሥራት አቅዷል? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ ከታዳሚያን ለተነሳው ጥያቄም ምክትል መሪው አንዱዓለም አራጌና ዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪው ኢዮብ መሳፍንት ምላሾቻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ኢዜማን በሚመለከት ለተነሱት ጥያቄዎች “በቂ ምላሽ በመስጠት ብዥታዎችን አጥርተናል” ሲሉ ኢዮብ መሳፍንት ለዜጎች መድረክ አስረድተዋል፡፡

ኢዜማ ከሲያትልና ሎስአንጀለስ በተጨማሪ በዋሽንግተን ዲሲ፣ ሳንሆዜ፣ ላስ ቬጋስና አትላንታ ሕዝባዊ ውይይቶችን ማካሄዱ የሚታወስ ነው፡፡ በመጪው ሳምንት መጨረሻ ደግሞ በዴንቨር እና ዳላስ ተመሳሳይ ስብሰባዎች ይደረጋሉ፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)


ጥቅምት 20 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የሠራተኛ ማኅበራት የሀገር ግንባታ ሚና

## የሠራተኛ ማኅበራት ዳራ

ዓለማችን የ”ሠራተኛ ማህበር” ከሚል ጽንሰ ሃሳብ ጋር የተዋወቀችው አውሮፓ ውስጥ የኢንደስትሪ አብዮት ተካሂዶ ጉልበቱን ለከበርቴው ሽጦ ኑሮውን የሚገፋና “ሠራተኛ” ተብሎ የሚጠራ የኅብረተሰብ ክፍል ከተፈጠረ በኋላ ነው። የካፒታሊስት ሥርዓት ሲጀመርም ሆነ ዛሬም ድረስ በውስጡ ከሚገኙ ዋና ዋና ግንኙነቶች ውስጥ አንዱና ትልቁ በሠራተኛውና በከበርቴው መደቦች መካከል ያለው ግንኙነት ነው። ይህ ግንኙነት ሠራተኛው በተከታታይ ባደረገው ጠንካራ ትግል እየለዘበና እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ሁሌም ለከበርቴው የሚያዳላ ግንኙነት ነው። በከበርቴውና በሠራተኛው መደቦች መካከል ያለው ግንኙነት የነፃ ገበያ ሥርዓትን ይከተላሉ በሚባሉ ሀገሮች ውስጥም ቢሆን ለከበርቴው የሚያዳላ ወገናዊ ግንኙነት ነው። ያለፉት ሁለት መቶ ሃምሳ ዓመታት የሠራተኛው መደብ የትግል ታሪክ በግልጽ እንደሚያሳየን የሠራተኛው መደብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅሙንና መብቱን የሚያስከብረው ከአሠሪዎቹ ጋር ቁጭ ብሎ መደራደር በሚያስችለው መልኩ ሲደራጅ ብቻ ነው። ዛሬ በብዙ ሀገሮች ውስጥ ሠራተኛው በሠራተኛ ማኅበራት ተደራጅቶ ባደረገው ትግል ከሚኖርበት ማኅበረሰብ የኑሮ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እራሱንና ቤተሰቡን ማኖር የሚያስችል ደሞዝ እንዲከፈለውና ሌሎችንም ጥቅማጥቅሞች ማግኘት ችሏል። ይህ በረጅም ጊዜ የተገኘ ድል ሠራተኞች የሚኖሩበት የፖለቲካ ማኅበረሰብ ሙሉ አባል ነኝ የሚል የባለቤትነት እና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲኖራቸው አድርጓል። ይህ የባለቤትነት እና በራስ የመተማመን ስሜት ደግሞ ለሀገር ሰላምና መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

የኢንደስትሪ አብዮት ተጀምሮ አውሮፓ ውስጥ ከኢንደስትሪ መስፋፋት ጋር ተያይዞ እያደገ የመጣው የሠራተኞች መደብ የመጀምሪያዎቹ አንድ መቶ ዓመታት ታሪክ ሠራተኞችን ገንዘብ የሚከፈላቸው የከበርቴው ባሪያ ያደረገ እንደነበር ታሪክ ያስታውሰናል። በእነዚህ ዓመታት የሠራተኞች መደብ ደሞዝ ለኑሮ የማይበቃ ዝቅተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የፋብሪካ ሥራ አንዳንዴ በሰዓት ያልተገደበ፣ ከበርቴው ሠራተኛውን ባሰኘው ጊዜ ሁሉ ከሥራ የሚያባርርበት ከመሆኑም በላይ የፋብሪካ ውስጥ የሥራ ሁኔታ እጅግ በጣም አድካሚና የሠራተኞችን ሕይወት ለአደጋ ያጋለጠ ነበር።

ምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ከ1870ዎቹ በኋላ እየተሻሻለ የመጣው የሠራተኛ ሕግ ሠራተኞች በማኅበር ተደራጅተው ለመብታቸው መታገል እንዳይችሉ ያደረጉትን የፖለቲካ እንቅፋቶች በማስወገዱ ሠራተኞች በማኅበር ተደራጅተው የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ ከጸጥታ ኃይሎች ጋር የሚያደርጉት ትግል የየቀኑ እንቅስቃሴ መሆን ጀመረ። እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1906 ዓ.ም በተከታታይ የተካሄደውና ግማሽ ሚሊዮን የሚደርሱ ሠራተኞችን ያሳተፈው የፈረንሳይ ሰራተኛ ማህበራት እንቅስቃሴ ከ1300 ጊዜ በላይ የስራ ማቆም አድማ ያደረገ ሲሆን ታላቋ ብሪታኒያ እና ጀርመን ውስጥም ተመሳሳይ የሥራ ማቆም አድማዎች ተደርገዋል። በ1909 እና በ1913 መካከል እንግሊዝ ውስጥ የተደረገውና ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሠራተኞችን ያሳተፈው የሠራተኛ ማኅበራት የሥራ ማቆም አድማ ሠራተኞች መብታቸውን ማስከበር የሚችሉ እንደሆነ ማሳየት ችሏል። ይህ የሠራተኞች ማኅበር ተደራጅቶ ከከበርቴዎች ጋር ለዓመታት ያደረገው ትግል የሠራተኞችን ደመወዝ ከማሳደግ ጀምሮ የሥራና የሥራ አጥነት ዋስትና፣ ብሄራዊ የጤና መድን አገልግሎት፣ ነጻ የትምህርት ዕድልና ሌሎችም ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶቹን ማስከበር እንዲችል አድርጎታል።

## ሠራተኛ ማኅበራት በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ውስጥ የፊውዳል የምርት ግንኙነት ለረጅም ዓመታት መዘለቁና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በአብዛኛው በኋላ ቀር ግብርና ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የሠራተኛ ማኅበራት እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ዘግይቶ ነው የመጣው። በ1948 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ለሠራተኞች የመደራጀት መብት የሰጠ ቢሆንም በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት የሠራተኞችን በሞያ ማኅበራት መደራጀት የሚፈቅድ የሠራተኛ ሕግ አዋጅ ያወጣው በ1954 ዓ.ም ሲሆን የመጀመሪያውና መንግሥት እውቅና የሰጠው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር የተቋቋመው በ1955 ዓ.ም ነው። በ1966ቱ አብዮት ዋዜማ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን (CELU) ወደ ሰማኒያ ሺ የሚጠጉ አባላት ያሏቸውን የተለያዩ 167 የሙያ ማኅበራትን ያቀፈ ድርጅት ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ የሠራተኛ ማኅበራት በቀዳማዊ ኃይለስላሴ፣ በወታደራዊው መንግሥት እና በሕወሃት/ኢሕአዴግ ዘመናት የነበሩ ቢሆንም ማኅበራቱ የመደራጀት፣ ሀሳባቸውን የመግለጽና መብታቸውን የመጠየቅ አንጻራዊ ነጻነት የነበራቸው በንጉሱ ዘመነ መንግሥት ብቻ ነበር። በደርግና በሕወሃት/ኢህአዴግ ዘመን የሠራተኛ ማኅበራት መንግሥት በሚፈልገው ቅርፅና ይዘት የተደራጁና የመንግሥት ዓላማ ማስፈጸሚያ መሣሪያዎች እንጂ የሠራተኞችን መብት ለማስከበር የሚሠሩ ድርጅቶች አልነበሩም።

የመላው ሀገራችን ሠራተኞች ከሀገራቸው ከፍ ባለ መልኩ ከዓለም አቀፍ እህት ማኅበራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ትግላቸውን ለማጠናከር ሠርተዋል፡፡ በተለይ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር (ኢሠማ)፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ)፣ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር (ኢጋማ) ከዓለምአቀፍ ሠራተኞች ማኅበር (Interna-

tional Labour Organiztion እና Education International) ጋር በጋራ በመሥራት ትግላቸውን ዓለምአቀፋዊ ባህሪ አላብሰውታል፡ ፡ Education Intrenational (EI) የተሰኘው ድርጅት በተለይ በሕወሃት/ኢሕአዴግ መንግሥት በመምህራን እና በሠራተኞች ማኅበር መሪዎች ላይ ይደርስ የነበረውን ከሥራ መባረር፣ መታሰር እና መገደልን በቅርብ ከመከታተል በላይ ይህ አምባገነናዊ ድርጊት እንዲቆም ከኢትዮጵያ የሞያ ማኅበራት መሪዎች ከጎን በመቆም ሀገር ውስጥ ድረስ በመገኘት መንግሥት ላይ ጫና ሲያደርግ የነበረ መሆኑ ሠራተኞች በማኅበራት የነበራቸውን አስተዋፅኦ አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ በተለይ የአቶ አሰፋ ማሩ በአደባባይ መገደል ጋር ተያይዞ እነዚህ የዓለምአቀፍ ማኅበራት ከኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ጎን ቆመው ድርጊቱን ማውገዛቸው የሚጠቀስ ነው፡፡

Eduction Internationale ወደ 24 ሚሊዮን የሚደርሱ አባል መምህራንን ያቀፈ ማኅበር ነው፤ ይህ ግዙፍ ማኅበር በመላው ዓለም በተለይም በአውሮፓና በአሜሪካን ሀገር በሚደረጉ ምርጫዎች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲያሳይ የኖረ ነው፡ ፡ በአብይነት የእንግሊዝ መምህራን ማህበር (National United Neacher (NUT)) ጠቅላይ ሚኒስተር ቶኒ ብሌር ወደ ሥልጣን ለመውጣት ያሰቡትን ጥያቄ መቀበል የቻሉት እና ድጋፍ ያደረጉት በኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ላይ የጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ መንግስት ተፅዕኖ እንዲያደርጉ የተጠየቁት ጥያቄ መቀበል በመቻላቸው ነበር፡፡

## የሠራተኛ ማኅበራት የሠራተኛውን ጥቅም ከማስጠበቅ ያለፈ ሚና

በሽግግር ሂደት ላይ የምትገኘው ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬም የኢኮኖሚ መሰረቷ ግብርና ቢሆንም የወደፊቱ አቅጣጫችን ግን ቀላልና ከባድ ኢንደስትሪዎችን በመገንባት ላይ የሚያተኩር ስለመሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም። ዛሬ ከአንድ መቶ ሚሊዮን በላይ የሚገመተውንና በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የሚሄደውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከግብርናው ዘርፍ አላቀን ወደ ኢንደስትሪውና አገልግሎት መስጫ ዘርፎች ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ካልቻልን የተረጋጋ ማኅበረሰብ መፍጠር ያስቸግረናል። ሀገራችን ውስጥ የኢንደስትሪና የአገልግሎት መስጫ ዘርፎች እድገትና መስፋፋትን ስናስብ በፍጹም መርሳት የሌለብን አንድ ትልቅ ጥያቄ ቢኖር የሠራተኞች መደብ መብትና ጥቅም እንዴት ይከበራል የሚለውን ጥያቄ ነው። አውሮፓና አሜሪካ ውስጥ የሠራተኞች መደብ በማኅበር ተደራጅቶ መብቱን ለማስከበር አያሌ ዓመታት ፈጅቶበታል። እኛ ኢትዮጵያዊያን ከአውሮፓና ከአሜሪካ መማር ያለብን የኢንደስትሪ ግንባታ ሂደትን ብቻ ሳይሆን የእነዚህን ሀገራት የሠራተኛ ማኅበራት የትግል ታሪክ ጭምር ነው፡፡

የሠራተኛ ማኅበራት ሚና ዛሬ ከደሞዝ ጭማሪና የሥራ ሁኔታ መሻሻል ጥያቄዎች አልፎ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አድማሱ እየሰፋ መጥቷል። ዛሬ አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራትን ጨምሮ በብዙ የዓለማችን ሀገራት ውስጥ የሠራተኛ ማኅበራት በኢኮኖሚ መስክ የሠራተኞችን መደብ የኑሮ ደረጃ እንዲያድግ በማድረግ፣ በፖለቲካው ዘርፍ ሠራተኞች ጥቅሞቻቸውን እና መብቶቻቸውን የሚያስጠብቁላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶችና ፖለቲከኞች ለይቶ እንዲያውቁ በማድረግና በማኅበራዊው ዘርፍ ደግሞ በከበርቴውና በሠራተኞች መደቦች መካከል ያለው ልዩነት እንዲጠብ በማድረግ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ። አሜሪካንን በመሰሰሉ ካፒታሊዝም በነገሰባቸው ሀገራት ውስጥ በምርጫ ወቅት የሠራተኛ ማኅበራትን ድጋፍ ማግኘት ምርጫውን የማሸነፍ ምልክት የሚሆንበት ጊዜ አለ። ይህ በፖለቲከኞችና በሠራተኛ ማኅበራት መካከል በምርጫ ወቅት የሚታየው መደጋገፍ ከምርጫው በኋላ የሠራተኛ ማኅበራትን ጡንቻ ማፈርጠም ወደሚችል ግንኙነት የሚያድግ ጠንካራ ፖለቲካዊ መደጋገፍ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ የሠራተኛ ማኅበራት ታሪክ ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ አስቆጥሯል። ሆኖም አብዛኛው ታሪኩ ከአምባገነን መንግሥታት ጋር የተሳሰረ በመሆኑ የመንግሥታቱ የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያ መሳሪያ ከመሆን አልፎ የሠራተኞችን መብትና ጥቅም ማስከበር ቀርቶ እራሱን በነጻነት ማደራጀትም አልቻለም። ስለሆነም ዛሬ በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ሠራተኞችን በየሥራ መስካቸው በአዲስ መልክ በማደራጀት ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነጻ የሆነና በነጻነት እራሱን በራሱ የሚመራ ሀገር አቀፍ የሠራተኛ ማኅበር ማቋቋም አስፈላጊ ነው። የሠራተኛ ማኅበራት የሠራተኞችን መደብ የኑሮ ደረጃ እንዲያድግ በማድረግና በማኅበረሰብ ውስጥ የሚታየውን ከፍተኛ የገቢ ልዩነት በማጥበብ ለሰላምና መረጋጋት መኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፣ የሰላምና መረጋጋት መኖር ደግሞ ለዴሞክራሲ እድገትና መስፋፋት ቁጥር አንድ ግብአት ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት የተከተለችው የፖለቲካ መስመር የተቃኘው በዘውግ ማንነት በመሆኑ የዛሬው የኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ዘውግ ላይ የተመሠረተ ፖለቲካን በሚያቀነቅኑና የዜግነት ፖለቲካን በሚሰብኩ ሁለት የተለያዩ ኃይሎች በሚያካሄዱት ትግል እየተተራመሰ ይገኛል። ይህ ትርምስ መልክ እንዲይዝ በማድረግና ዜጎች ራሳቸውን በዘውግ ማንነታቸው ብቻ ሳይሆን በሌሎች የተለያዩ ማንነቶቻቸው እንዲያዩ መንገድ ከሚከፍቱ ተቋሞች ውስጥ የሠራተኛ ማኅበራት ግንባር ቀደሞቹ ናቸው። የፋብሪካ ሠራተኞች፣ መምህራንና የአገልግሎት መስጫ ዘርፍ ሠራተኞች በማኅበር ተደራጅተው የፖለቲካ፣የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን ለማስከበር ሲታገሉ የሚያገናኛቸውና ለአንድ ዓላማ የሚያሰልፋቸው ዘውግ ወይንም ቋንቋ ሳይሆን የጋራ የሆኑ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅሞች ናቸው። ይህ እውነት የሚነግረን ሀገራችን በኢንደስትሪ እድገት ወደፊት በገፋችና የሠራተኛ ማኅበራት በዓይነትና በመጠን ባደጉ ቁጥር በአንድ በኩል ዛሬ ሀገራችን ውስጥ በስፋት የሚታየው የማንነት ፖለቲካ ጡዘት እየረገበ ሊመጣ እንደሚችልና በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከዋልታ ረገጥ ኃይሎች ነጻ እየወጣ የማዕከል ፖለቲካነት ባህሪይ እየተላበሰ እንደሚመጣ ነው። ባጠቃላይ የዓለም ሠራተኛ ማኅበራት የረጅም ግዜ ትግል ታሪክ የሚነግረን ነገር ቢኖር የሠራተኛ ማኅበራት የሠራተኞችን ጥቅም ከማስከበር አልፈው ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር በማድረግ ለዴሞክራሲ እድገትና ለሀገር ብልጽግና ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ነውና የኛም ሀገር ሠራተኛ ማኅበራት ተመሳሳይ ሚና መጫወት እንዲችሉ ተደርገው በነጻነት የሚደራጁበትን መንገድ ለማዘጋጀት ፓለቲካ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማኅበራት፣ መንግሥትና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት።

# ኢዜማ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ

## “የኢትዮጵያ ሕዝብ ለቀረበለት ሀገርን የማዳን ጥሪ በኅብረት መልስ መስጠት የሚገባው ወቅት ዛሬ ነው!”

ጥቅምት 18/2012 ዓ.ም




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) “የኢትዮጵያ ሕዝብ ለቀረበለት ሀገርን የማዳን ጥሪ በኅብረት መልስ መስጠት የሚገባው ወቅት ዛሬ ነው!” በሚል ርዕስ 8 ነጥቦችን ያቀፈ ጋዜጣዊ መግለጫ ጥቅምት 18 ቀን 2012 ዓ.ም በዋና ፅ/ቤቱ ሰጠ፡፡

ጋዜጣዊ መግለጫው ትኩረቱን ያደረገው ሰሞኑን ባጋጠመው ሕገ ወጥ ተግባራት የተሳተፉ ግለሰቦች እና ቡድኖች ከፖለቲካው ወገንተኝነት በፀዳ መልኩ በአግባቡ ለፍርድ እንዲቀርቡ፤ በተከሰተው ረብሻ ምክንያት የተፈናቀሉት ወገኖች ትኩረት እንዲሰጣቸው፣ መንግሥትም ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሚያሳስብ ነው፡፡ ራስን ለመከላከል እንደ ማኅበረሰብ አቀፍ ፖሊስ የመሳሰሉ ሕጋዊ አደረጃጀቶች በአስቸኳይ ማጠናከር እና ሥራ ላይ ማዋል እንደሚገባ በመግለጫው ተወስቷል፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ለቀረቡት ጥያቄዎችም የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)፣ የፓርቲው ሊቀ መንበር የሺዋስ አሰፋና ዋና ጸሐፊው አበበ አካሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ኢዜማ በመግለጫው መጨረሻ ላይ ለፓርቲው አመራሮች፣ አባላት፣ ደጋፊዎችና ለሕዝብ መረጋጋትና አስተውሎ መንቀሳቀስ ወሳኝ መሆኑን፣ ይሄንንም ሥራ ላይ እንዲያውሉት አደራ በማለት ከአምባገነናዊ ሥርዓት ለመውጣትና ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ሀገር አድርጎ ለማስቀጠል ከሚሹ ወገኖች ሁሉ ጋር በጋራ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን በማሳወቅ ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ ለሀገር በቀል ማኅበራት፣ ለሀገር ሽማግሌዎች፣ ለሃይማኖት አባቶችና ለሌሎችም የማኅበረሰብ መሪዎች የሀገር እናድን ጥሪ አቅርቧል፡፡

# ኢዜማ ምርጫ ወረዳ 25 ከነዋሪዎች ጋር ተወያየ

ጥቅምት 20 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምርጫ ወረዳ 25 ጥቅምት 16 ቀን 2012 ዓ.ም ሕዝባዊ ስብሰባ ማካሄዱን የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 25 ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ደምሳሽ በኃይሉ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

በሕዝባዊ ስብሰባው ላይ የምርጫ ወረዳ 25 የኢዜማ አባላት፣ ሥራ አስፈፃሚዎች፣ የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲሁም የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ተገኝተው በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መምከራቸውን ኃላፊው አስረድተዋል፡፡በውይይቱላይከተነሱትሀሳቦች መኻል ፀጥታና ሰላምን ከማስጠበቅ አንፃር የዜጎች ኃላፊነት ምን መሆን እንደሚገባውና ዜጎች ከወረዳቸው አንስቶ እስከ ከፍተኛ የመንግሥት መዋቅር ድረስ በመረጡት ሰው ለመተዳደር ከዜጎች ምን ይጠበቃል የሚሉ ሀሳቦች ይገኙበታል፡፡ በስብሰባው ላይ ከ400 በላይ ተሳታፊዎች መገኘታቸውን የጠቆሙት ኃላፊው በተደረገው የሀሳብ ልውውጥ የወረዳ 25 ነዋሪዎች እውቀትና ግንዛቤ እንዳገኙበት አስረድተዋል፡፡ በእለቱም በርካታ ነዋሪዎችን ለአባልነት መመልመል እንደተቻለ ኃላፊው ገልፀዋል፡፡